## <u>የአህያ ባል ከጅብ አያስጥል፦</u>

የትግራይ ወራሪ ቡድን ወደ ማሐል አገር ገብቶ የመንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ኢትዮጵያን የመበታተን ዓላማውን ስኬታማ ለማድረግ በርከት ያሉ የጥፋት መንገዶችን መከተሉ ይታወቃል ከነዚህም አንዱ ክፍለ ሀገር ይባሉ የነበሩትን ወደ ዞን ፤አውራጃ ይባሉ የነበሩትን ወደ ወረዳ በማሳነስ ሦስትና አራት ዞኖችን ወደ ክልል(ስቴት) በማዋቀር በየመንደሩ ትናንሽ መንግሥታትን አስቀምጦ በበላይነት እየገዛ ለሃያ አምስት አመታት ቀጥሏል።

እነዚህም የኦሮሞ ክልል፤የአማራ ክልል፤የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል፤የሐረሬ ክልል፤የጋምቤላ ክልል፤የቤንሻንጉል ክልል፤የአፋር ክልል፤የደቡብ ክልልና የትግራይ ክልል በመባል ይታወቃሉ።በወረቀት ላይ ብቻ ተፅፎ በቀረው የሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት ላይም የሥልጣን ገደባቸው፤የግዛት ክልላቸው ተለይቶ ለይስሙላ ተቀምጦ ይገኛል።ያ ሁሉ ማምካሸትና ኢትዮጵያውያን በጉጉት ይጠብቁት የነበረውን አንድነት፤እኩልነትና ነፃነት፤የብሄር ብሔረሰቦች እኩልነት፤የልማት በለቤትነት፤የዜጎች እኩልነት በሞቀ አዳራሽ በአሰረሽ ምችው በትላልቅ አፈ-ጮማዎች ተነግሮ ኢትዮጵያውያን ከአዳራሹ በተገባላቸው ቃል መሠረት እናገኛዋለን ብለው ይጠብቁት የነበረው ተስፋ የእርጎ ባሕር ሆኖ እንደቀረባቸው ዛሬ ላይ ሆነው ሳያስታውሱት አይቀሩም።

ወራሪው የትግራይ ተገንጣይ ቡድን <u>«ጅብ እስኪይዝ ያነክስ»</u> እንዲሉ የእያንዳንዱን ልብና አቅም እስኪመረምር ድረስ ጊዜ ገዝቶ ጨዋታውን እያዳመቀ ቆይቶ በኋላ ግን እጅ መጠምዘዙን ጀመረ። በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ማንኛቸውንም መንግሥታዊ የሆኑና ያልሆኑትን መዋቅሮች የሚቆጣጠር፤ፈቃድ የሚሰጥና የሚነፍግ ኃይል ከወራሪው የህወሃት ቡድን እየተመለመለ ከያንዳንዱ የክልል ባለሥልጣናት አናት ላይ ፊጥ አለበት።ያጉረመረመ ባለሥልጣን እንደ አሮጌ ቁና መወርወር መታሰር መሰደድ እጣ-ፈንታው ሲሆን ከአምበሳው ድርሻ የሚረግፈውን ለቅሞ ለማደር የመረጠው ደግሞ ራሱ ተረግጦ የመረጠውን ሕዝብም እያስረገጠ ቀጠለ።

ሕዝብ አፈና ሲበዛበት መብቱ ሲረገጥ ዘመናት ያስቆጠረው የውስጡ ሕመም ገንፍሎ ሲወጣ የሚመልሰው እንደማይገኝ ቢታመንም በኃይል ረግጠን እንገዛዋለን፤እንዘርፈዋለን በአጠቃላይ አነጋገር እኛ ከምንለው ውጭ አንድ ስንዝር ሊያልፍ አይገባውም ብለው <u>«እንደሞፈር አርቀው እንደ እርጉዝ አስጨንቀው»</u> ሊገዙት የሚያስቡት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየአቅጣጫው የመብት ጥያቄዎችን እያነሳ ከራሴ ላይ ውረዱ ማለት ጀምሯል።ይህ ደግሞ አግባብ ባለውና በሰለጠነ ሁኔታ ሊፈታ ሲገባው የመፍትሔ አሰጣጡ ሁኔታ ከኃይል የዘለለ አይደለም።በተለይም የህወሃት በማንኛውም ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ክልሎች መብታቸውን አሳልፈው በመስጠት በሕዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለው አስከፊ ድርጊት የክልሉ ባለሥልጣናትን ትልቅ ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው ከወዲሁ ሊገነዘቡት ይገባል።

<u>የአህያ ባል ከጅብ አያስጥል እንድል ያደረገኝም ይኸው ድርጊታቸው ነው።ከእንስት አህያ ጋር የሚሄድ ጅብ እንስቷን አህያ ጅብ ሲያንከባላት ተባቱ አህያ ማዳን አይችልምና። የየክልሉ ባለሥልጣናትም የዚህ ቀጥተኛ አባባል ምሳሌ ናቸው።</u>ከትግራይ ክልል ውጭ ያሉት 8 ክልሎች ከሽግግር ዘመኑ ወዲህ እስከ አሁን ድረስ እየፈፀሙት ያለው ይኸውን ነው።ይህ ግን ወደ ፊት የማይቀጥልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በአማራ ክልል ፤ጋምቤላ ክልል፤በኦጋዴንና በአፋር ክልሎች የተፈፀመውና እየተፈፀመ ያለው ዘር የማጥፋትና ዘር የማጽዳት ፋሽስታዊ ርምጃ በጀመረው እንዲቀጥል የሚያደርግ እድል ከአሁን በኋላ አይኖርም።

ሕዝቡ ከየአቅጣጫው በመነሳሳት የራሱን የጎበዝ አለቆች እየመረጠ ራሱን በራሱ ማስተዳደር ጀምሯል፦ ለምሳሌ በሰሜን ጎንደር የቃብትያ ወረዳ፤በቅርቡ በዳባት ፤በየዳ የመንግሥት ባለሥልጣናትን አባሮ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ቆርጦ መነሳቱና በሌሎች አካባቢዎችም የዚህ ተዛማጅ ጅማሮች መከሰታቸው አንድ

*በግልጽ ልናየው የምንችለው ነገር ቢኖር አምባገነኖች የሕዝብን እምቢተኝነት በመሣርያ ኃይል አፍነው በኃይል ሊገዙ የማይችሉ መሆኑን ነው።እንደ ህወሃት ዘላቂ ግብ ወይም ስትራቴጅ ከሆነ አንዱን ሃይማኖት በሌላው አንዱን ጐሣ ከሌላው ጐሣ ጋር በማጋጨት በዋናነት ደግሞ ከአማራ ብሔር ውጭ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች በአማራው ላይ ጥላቻ እንዲያሳድሩ በማድረግ ብዙ ርቀት የተሄደበት ነበር።ይሁን እንጅ ይህ ተግባር በራሱ ህወሃትን የሚያጠፋና ከሕዝብ የሚነጥል ሆኖ እናገኘዋለን።*

*የኢትዮጵያ ሶማሌዎች ክልል ህዝብ አማራ ጠላትህ ነው ተብሎ ተሰበከ እውነት መስሏቸው አብረው ከህወሃት ዘረኛ በሽታ ጋር ነጐዱ ህወሃት ራሱ እንደ እባብ ሲቀጠቅጣቸው የድረሱልኝ ጥሪ አሰሙ፤ የጋምቤላ፤የአፋሩ ሁኔታም ተመሳሳይ ነው።በአማራና በኦሮሞ መሀከል ያለውን ግንኙነትም እየከፋ እንዲሄድ ህወሃት ያልጫረው ጉድጓድ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም።ይህ ብቻውን ሳይሆን በአንዳንድ እንደ ኦነግና ኦህዴድ በመሰሉ ድርጅቶች ብዙ ድካም ቢደረግም የአማራና የኦሮሞ ብሔሮች በተለይ ወጣቱ ትውልድ እጅ ለእጅ ተያይዞ ጣቱን በህወሃት ላይ ቀስሮ ትግሉን አጠናክሮ ሥርዓቱን ለማስወገድ እየታገለ ይገኛል።*

*ህወሃት ወደ መሀል አገር ለመግባት እድል የፈጠሩለትን በአምሳሉ የፈጠራቸውን ድርጅቶች መፈታተን አሁን የተጀመረ ባይሆንም የአሁኑ ግን ያፈጠጠና በግልጽ ጣልቃ ገብነቱን እያሳየ ነው። ለህወሃት የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የአማራ ብሔር ማንነት ጉዳይ ብርክ የሚያስይዝ ጥያቄ ቀርቦ ጥያቄውን ሕጋዊ መልስ መስጠት ሲገባ በኃይል አዳፍኖ ለመሄድ እየታየ ያለው የችግር አፈታት ዘዴ ነገሮችን ወደ አላስፈላጊ ደረጃ እየወሰደ ያለ መሆኑ እየታወቀ ለቅማንቶች ጥብቅና መቆም ህወሃት በማንኛውም አጋጣሚ በአማራ ላይ የሚነሳ ካለ እንደ አንድ መልካም ነገር በማየት ነገር ለማባባስ እረፍት የሌለው መሆኑን በድጋሚ እንድናውቀው አድርጓል።።*

*ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ህወሃት ትውልደ ትግራይ የሆኑ አማርኛን በደንብ አበጥረው የሚናገሩ ወይም በዚሁ በአማራ ክልል የተወለዱትን ፀረ-አማራ አቋም በማስያዝ ከዛሬ ጀምሮ እናንተ አማራዎች ናችሁ ብሎ በመሰየም በመከላከያ ኃይሉና በብአዴን ውስጥ የሰገሰገ ሲሆን የአማራ ክልል ውስጥ ብቻ የአገው ኽምራ ዞን፤የአገው አዊ ዞን፤የባቲ ኦሮሞች ዞን የሚባሉትን አሁን ደግሞ በብአዴንና በህወሃት በካከል ግጭት ሊያስነሳ ይችላል ተብሎ የወቅቱ መነጋገርያ የሆነው ህወሃት ቅማንቶችን በማስታጠቅና ደጀን በመሆን ሰሜን ጎንደር ለቅማንቶች ይገባል የሚል አቋም ሲይዝ የአማራ ክልል ተጠሪና የክልሉ ምክር ቤት ቅማንትና አማራ ተዋልደው አንድ ሆነው በጋራ ታሪክ ያላቸው ስለሆነ ጥያቄው አግባብ የለውም የሚል ጉዳይ ቢኖርም የማንኛው አቋም ገፍቶ ተግባራዊ እንደሚሆን የምናይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።*

*በአጠቃላይ ሥርዓቱን በዚህ ዙርያ ስንመለከት ከላይ እስከ ታች በሙስና የበከተ፤የሁሉም የመምራት አቅም ተሟጦ ሥርዓት አልበኝነት እየተስፋፋ ሕዝቡ ራሱን በራሱ እየመራ የሚገኝበት ወቅት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።ለሥርዓቱ እድሜ መራዘም ሲባል በብዙ ስም መጠርያ የተሰጠው ጠምንጃ አንጋች በአስተዳደርና በሕዝብ ጉዳይ ገብቶ ማየት ማለት ምንን እንደሚያመላክት ይታወቃል።በውጭ ኃይሎች ታገዘም አልተገዘ ይህ ሥርዓት ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ አጀንዳ ያለው ስለሆነ መወገድ አለበት።እንዴት ሊወገድ ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል?ጀግኖች ወላጆቻችን እንዴት ይህችን አገር ጠብቀው አቆዩን ?የሚል ጥያቄ ላንሳና ይህ የዘመኑ የእኔ አይነቱ ትውልድ ለምን አይጀግንም?እንዴት ሁሉም ለሥልጣን ይቋምጣል?የሀገርና የሕዝብ ሀብት ለመዝረፍስ ለምን ይነሳሳል?ቂምና ጥላቻ ብቀላን አርግዞ አገሬ ኢትዮጵያ እያሉ መቆዘም እንዴት ይቻላል?*

*ከገዥው ቡድን አንዲት የሰናፍጭ ፍሬ ያህል በጎ ነገር ባይጠበቅም የሥርዓቱ ተቃዋሚዎች የኢትዮጵያ ዜጎች በየደረሰበት እንደ በግ እየታረዱ ለዚያ ችግር መድረስ እየተገባ እርስ በእርስ መናከስ፤መወነጃጀልና*

*አንዱ ሌላውን ጠልፎ ለመጣል መሽቀዳደም ምን አመጣው?ህወሃት የሚፈራው አንድነትን ነው ብለናል ይህ ከሆነ ለምን አንድነት ፈጥረን ህወሃትን በፍርሃት በቀቀን እርስ በእርሱ እንዲተረማመስ አናደርግም?ገና ከወዲሁ ከህወሃት የማይሻሉ ሆነው ለመዝለቅና የሥልጣን ኮረቻ ላይ ለመውጣት ፖለቲካውን መሬት ላይ ወርዶ ቁርና ሀሩሩን፤አቀበት ቁልቁለቱን፤ርሃብና ጥማቱን፤መሞትና መዳን ባጠገቤ ሳይደርስ ሕዝቡን በማነቃነቅ ሕዝብ በሚከፍለው መስዕዋትነት ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ትግሉን በሪሞት የሚመሩ ማፈሪያ የሌላቸው ፖለቲከኞችን የሚተባበሩና አብረው የሚመከሩ ኢደብ ቢገዙ የተሻለ ይመስለኛል። በተለይ ዲያስፖራው ሰላም በሰፈነበትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በዳበረበት አገር እየኖረ ዘላቂነት ለሌላቸው ድርጅቶች ኪሱን ከማራቆት አልፎ በወገኖቹ ላይ እሳት ለማንደድ እየተደረገ ያለው መንደፋደፍ እንዲያቆም እያንዳንዱ ራሱን ሊፈትሽና ከድርጊቱ ሊቆጠብ ይገባዋል ብየ አምናለሁ።*

*በቴሌ ኮንፈረንስ ፤ በፓል ቶክ የሚደረጉ ውይይቶች አልፎ አልፎ ገባ ብየ ሳዳምጥ፤በራዲዮና ቴሌቪዥን በእንግድነት ተጋብዘው ንግግር የሚያደርጉ ግለሰቦችን ስሠማ ኢትዮጵያዊነታቸው ተሟጦ ጠፍቶ አገር ወራሪው ህወሃት ከሚፈጽመው ክህደት የተሻለ እንዳልሆነ በተጨባጭ አረጋግጫለሁ።ምናልባት አንታወቅም በሚል ምክንያት ተደብቆ ለመናገር ታስቦ ሊሆን ይችላል።በፍፁም በፍፁም አንድም ሚስጥር ተደብቆ እንደማይቀርና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ሊያጋልጧችሁ እንደሚችሉ ከወዲሁ እንድታውቁት መናገር እወዳለሁ።*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!*

*አንተነህ ገብርየ*